# አሟሟትና ሞት

አብርሃም በየነ

ሲሞቱ እንደ ቴድሮስ ውርደት ተፀይፎ

የታሪክ አሸራ በደም ቀለም ፅፎ

ሞትን ይሞቱታል ባሟሟት አግዝፎ

ከሽጉጡ አፈሙዝ ጥማቱን አርክቶ

ከመቃብር በላይ የሚውል ስም ትቶ

ሞትን ይሞቱታል በሞት ታሪክ ሰርቶ

ሞትን ይሞቱታል ከሞት የለም ቀሪ

ግን ሀውልት የሚሆን ያፅሙ ስብርባሪ

አሟሟት ብቻ ነው የታሪክ ፈጣሪ

ድንገት ሲከበቡ ደርሶ በሞት ጥላ

አሟሟት ከቴድሮስ ወርሶ በመሃላ

እንደ አያሌው ባንገት ጥላሁን በገላ

ሞትን ይሞቱታል

ተንሰዬን አድርጎ ኪንፋዝን መቅደላ።

መስከረም 2005